# **ዐማራ ነኝ!**

ከመስፈሪያ ሚዛን እጅግ የበለጥኩኝ፤

ከሰፋሪ መዛኝ በጣሙን የላቅኩኝ፤

ማተቤን ያጠበኩ ፍቅርና ክብርን ደርቤ የያዝኩኝ፤

ኢትዮጵያን ቆርቋሪ ወደር አልባ ኩሩ አዎን ዐማራ ነኝ!

የከርስና የሆድ ስፋት፤

የለየሁኝ ገና በጧት፤

ከርሴ ጠቦ ሆዴ ሰፊ የሆነልኝ፤

የማስተውል እውነት ፈራጅ ዐማራ ነኝ!

ሩህሩህ ነኝ አጉራሽ አርሶ፤

ሿሚ ሻሪ አንጋሽ ነግሶ ፤

ከኔ ይልቅ ላንተ ያልኩኝ፤

በፍቅር ያለሁ ዐማራ ነኝ!

ከቀደሙት የባንዳ ልጅ ባንዳዎቹ፤

ከዘመኑ አንፏቻሪ ሹምባሾቹ፤

ያልወገንኩኝ ውሀቸውን ያልጠጣሁኝ፤

የተለየሁ ወርቀ ዘቦ ዐማራ ነኝ!

ታደልኩ እንጂ በአንድዬ፤

መቼ ታገልሁ እንዴት ብዬ፤

ሁሉ ሞልቶ የተቸረኝ፤

እንቁልልጭ ከማር የጣምኩ ዐማራ ነኝ!